ከዚህ አኳያ ሕግን ከመደቦች ግንኙነትና ዘዚህም ግንኙነት ሳቢያ ከሚመነጨው የአንድ መደብ ጥቅም ማስከበሪያ መሣሪያ ከሆነው ከመንግሥት ፣ ከመደቦች በላይ ልዕልና ያለው ገለልተኛና ከመለኮታዊ ስጦታ የሚመነጭ አድርጎ መገመት ፍጹም የተሳሳተ ነው::

<u>ሕገ መንግሥት፣</u> ማለት በቀላል አነጋገር የአንድ አገር ከፍተኛውና መሠረታዊው ሠነድ ነው:: የሌሎች ሕጎች ሁሉ መፍለቂያ ምንጭ ዋናው የመንግሥት ሕግ ነው::

ሕገ መንግሥት የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ ነው:: ሌሎች ሕጎች የሚወጡት በሕገመንግሥቱ ይዘት ላይ ተመሥርተው ስለሆነ ሕገ መንግሥት የሕጎች ሁሉ ምንጭ ይባላል:: ስለሆነም መሠረታዊ ሕግ ነው::

ሕግን ከመደቦች ሥርዓት ውጭ ለማየት የማንችለውን ያህል ሕገ መንግሥትም በተመሳሳይ በዚሁ ሥርዓት ውስጥ የሚታይ ነው::

ሕገ መንግሥት በመደቦች ትግል ውስጥ የመደቦችን የኃይል አሰላለፍ የሚገልጽ በኢኮኖሚው ሥርዓት ውስጥ የበላይነት ያለውን መደብ ጥቅም በበላይነት የሚያስከብር በአንድ ኅብረተሰብ የዕድገት ታሪክ ውስጥ የሚዋቀረውን መንግሥት አካል ቅርጽ የሚደነግግና መላ ኅብረተሰቡም ከዚሁ የመንግሥት አካል ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የሚያሰምር ሕግ ነው::

<u>የሕገ መንግሥት ሚና ፣</u>


ሕገ መንግሥት የገዥው መደብ ሕልውና ማስከበሪያ የመንግሥቱ ሕጋዊ ሕልውና ማረጋገጫ ነው::

ስለሆነም <u>የገዥው መደብ መሣሪያ ሆኖ ማገልገሉ አጠቃላይ ሚናው</u> ነው::

ሕገጋተ መንግሥታትን በአጠቃላይ፣ የሶሻሊስት ወይም ይሁን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮችን ሕገጋተ መንግሥታት በተለይ በመመልከትና ዘርዘር ያሉ መሠረተ ሃሳቦችን በመጥቀስ ይበልጥ ስለሕገ መንግሥት የተሟላ ግንዛቤ ማግኘት ይቻላል::

...//6

...//7


ሊገረሰስ ችሏል ። በዚህ መሠረት በ፲፱፻፷፮ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አብ
ልና በር ሊከፍት በቅቷል ።
ት ወቅት የተደራጀ ግንባር ቀደም አመራር ሰጪ አካል ስላልነበረ ፡ የሠርቶ
መለዮ ለባሹ ክፍል የተውጣጣው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ትግ
መረ ። ከዚያም የዘውድ አገዛዝን በማስወገድና በተከታታይ ልዩ ልዩ አብዮ
ለአዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት መሠረት ጣለ ። የገጠር መሬት ፣ የከተማ ቦታና

የሶሻሊስት ህገ መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው በሶቪየት ኅብረት ከታላቁ የጥቅምት [illegible]ስት አብዮት በኋላ ሲሆን ይህ ሕገመንግሥት በዚህ ጊዜ ዴሞክራሲ የሚያረጋግጥና የወዛደሩ [illegible]ነትን የሚያሰፍን የመጀመሪያ እውነተኛ ሕገ መንግሥት ነበር።

የሶሻሊስት ህገ መንግሥት የሚሠራጠቸው መርሆዎች ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ንቁ የሕዝብ [illegible]ትፍ ወዛደራዊ ዓለም አቀፋዊነት በሶሻሊስት ህጋዊነትና የኮሚኒስት ፓርቲው በመሪነት ሚና ና [illegible] በሶሻሊስት ሕገ መንግሥት ረቂቅ ላይ ሕዝቡ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ብቻ ሣይሆን በመጠረ[illegible] ድምፅ በመሥጠት ያፀድቀዋል።

— [illegible]ቀው በኋላ በራሱ ፍላጎትና ተሳትፍ የፀጠ እንደመሆኑ ለተገጠራዊነቱና ለተፈጻሚነቱ ያልተ[illegible] አስተዋፅኦ ያደርጋል።

— በሶሻሊስት ሥርዓት መንግሥታዊ አስተዳደር ለጥቂት ግለሰቦች እንደተሠጠ ፀጋ የሚቆጠር ሣይሆ[illegible] ሥርቶ አደሩ ሕዝብ የሚሣተፍበት ነው።

— [illegible]ሻሊስት አገሮችን ልምዱ በመቅሰም የሶሻሊስት ዕድገት ጉዳና የተከተሉና ነገር ግን የዕድ[illegible] ደረጃቸው ደግሞ የሶሻሊስት መንግሥትን ወዲያውኑ ለመመሥረት የሚያስችል ሁኔታ ላይ ያሉ አ[illegible]ሮች የሚቀርጹት ህገ መንግሥት የሚመደበው ከሶሻሊስት አገሮች ህገ መንግሥት ጋር ተመሳሳይ [illegible]። ምክንያቱም የዕድገት ደረጃቸው ይለያይ እንጂ መሠረታዊ ዓላማቸውና ግቡቸው አንድ [illegible]መሆኑ ነው።

እንደሚታወቀው በሶሻሊስት የዕድገት ጉዳና የሚጓዙ አገሮች ያሉቸው ኢኮኖሚ ቅይጥ ነው። [illegible]ህም ማለት የመንግሥት የሕዝብ የኅብረት ሥራ ማህበራትና የግል የኢኮኖሚ ይዞታ ያለበት በመሆ[illegible]። ይህ ቅይጥ የኢኮኖሚ ይዞታ ደግሞ የተለያዩ መደቦችንና የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያ[illegible]ል።

ስለሕዲሪ ረቂቅ ህገ መንግሥት ይዘት አጭር ማብራሪያ

ረቂቅ ህገ መንግሥቱ የያዛቸው ጥቅል ጉዳዮች 1/ መቅድመ በክፍል አንድ ሥርዓት ማህበር [illegible]ፍል ሁለት ዜግነት ነፃነቶች መብቶችና ግዴታዎች ክፍል ሦስት የመንግሥት አወቃቀርና አሠራር [illegible]ፍል አራት ጠቅላላ ድንጋጌዎች አካትተዋል።

ይህ ረቂቅ ሕገ መንግሥት ሲቀረጽ የሀገሪቷን ፖለቲካዊ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን [illegible]ሀገሪቷን ታሪካዊ አመጣጥ የዓለም አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታዎችንም አገናዝቦ የተዘጋጀ ሠነድ ነው።

ሕገመንግሥቱም ሲቀረጽ ከዚሁ ሁኔታ የሚመነጨውን መደባዊ ጥቅር ይ በማገናዘብ በዴሞክራሲያ[illegible] በህርያው መሰረቱን ሠርቶ አደር የሚወክል ይሆናል።

በዚሁ ሕገ መንግሥት ላይ ተመሥርቶ የሚቋቋመው መንግሥት የሠራተኛውን የገበሬውን መ[illegible]ደቦች እንዲሁም የመሰረቱን ሠርቶ አደር መደብ ጥቅም የሚያስጠብቅ ነው።

የዚህ ዓይነት ህገመንግሥት ለሠርቶ አደሩ መብቶች የቆመ ነው እነዚህ መብቶች በቋሚ ፕ[illegible] ሕጋዊ ሁኔታዎች የተደገፈ ቀጣይነትና ያላቸው ሲሆኑ የዜጎች መብቶችና ነፃነቶች በብዙ መ

ስለ ኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት አጭር

ቅኝት፤

የአሠራጫው የትምህርት፣ የቅስቀሳና

ፕሮፓጋንዳ ኮሚቴ፤

ሰኔ 1978 ዓ.ም

ገጽን፤

ረበስ ችሏል ። በዚህ መሠረት ... በከፈሉት ከፍተኛ

[illegible]ነማመን፣ ማብት በሕገ መንግሥት ውስጥ ከሚሰፈሩት የመብትና የነፃነት አንቀጾች ዋና ዋናዎቹ [illegible]።

ከዚህ በቀር ጾታ ሃይማኖት ብሔረሰብ የትም/ደረጃ ማህበራዊ ደረጃና ይኸን ሳይለይ ሁሉም [ዜጎ]ች በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን ተመሳሳይ መብትና ግዴታ ያላቸው መሆኑን ሕገመንግሥቱ በሚገባ [ያረጋ]ግጋል።

ሕገ መንግሥቱ የተጠቀሱ ግዴታዎች የህገሪቱ ዜጎች በአዲሱ ኅብረተሰብ ከግንባታ የተገኙትን [ድሎ]ች ከውስጥና ከውጭ ጠላቶች የመከላከል ለወደፊትም ለተጨማሪ ድሎች በሚደረገው ትግል ሙሉ ተሣ[ትፎ]ና ሁለገብ ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ይጠቅሳል።

[ብ]ሔረሰቦች ወንድማማችነት የሚደረገው ትግል በውጭ ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን በአገር ውስጥ የሚገለጽ [መሆ]ኑን በአገር ውስጥ በብሔረሰቦች መካከል ልዩነት የሌለ መሆኑ የሁሉም ብሔረሰብ አባላት በዜግ[ነ]ታቸው እኩል የሚታዩ በመሆናቸው በኢኮኖሚ በፖለቲካና በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች በእኩልነት ይሣ[ተፋ]ሉ።

የኢሕዲሪ ሕገመንግሥት በአገር ውስጥ ለሚመጡ ሌሎች ሕጎች አዋጆች ደንጋጌዎች መመሪያዎችና [illegible] ማስታወቂያዎች ሁሉ ምንጭ የሆነ መሠረታዊ የሕግ ሠነድ ነው።

ዛሬ በአብዮታችን ሂደት በተቀዳጀናቸው ድሎች ምርኩዝነት ሕዝባዊት ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊ[ክ] [ኢ]ትዮጵያን ለመመሥረት ጠር ከፋች የሆነውን ረቂቅ ሕገ መንግሥት በሕዝባዊ ውይይት መድረክ ሠ[illegible] አደሩ ሕዝብ በውይይቱ ወቅት ንቁ ተሣትፎ በማድረግ በቂ ግንዛቤ አግኝቶ አዳብሮ አስተያየ[ቶ]ች በሚሠጥበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። እስከአሁን በተጎናፀፍናቸው ድሎች ላይ በመመሥረት ለወ[ደፊ]ት ዓላማቸው ግቡ መምታት ሠፊው ሕዝብ ሙሉ በሙሉ የሥልጣኑ ባለቤት ለማድረግ ሕጋዊ ዋስት[ና] [የ]ሚሰጠን ሠነድ ሕልውና ማግኘት አያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ ከዜግነ[ት] የሚመነጭ መብትና ግዴታው ነው።

ሕዝባዊት ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ

ኢትዮጵያን እንመሠርታለን!!

ከጓዱ መንግሥቱ ኃ/ማርያም አመራር ጋር ወደፊት

ረቂቅ ሕገመንግሥትን ለማጳበርና ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን ለመመሥረት የሕዝቡ ቊኔትና ወሳኝነት ስለው፤

በአገራችን የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ቀጥተኛ የሥልጣን ባለቤትነት የተረጋገጠበትን መንግሥት የመመሥረት ዓላማ ከአብዮቱ መቀጣጠል ጋር ተያይዞ የመጣና ከፍተኛ ትግል ተደርጎበት መስዋዕትነትንም የጠየቀ መሆኑ ተደጋግሞ የተገለፀና በሁሉም የሚታወቅ ነው::

ባለፉት የአብዮቱ ዓመታት የተወሰዱት እርምጃዎችና የተመዘገቡ የድል ውጤቶች ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልካቸው የሕዝቡን የሥልጣን ባለቤትነት የሚያረጋግጡ ወይም ወደዚሁ መሠረታዊ ግብ የሚያደርሱ መሆናቸው የሚያጠያይቅ አይደሉም::

ተደጋግሞ እንደተወሳውና ታሪክም እንዳረጋገጠው የማንኛውም አብዮት ቁልፍ ጥያቄ የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ ነው:: ስለሆነም ለዚህ አብይ የፖለቲካ ሥልጣን ጥያቄ የተሟላ ምላሽ ማግኘት በየፈርጁ የተደረገው ትግል የተከፈለው መስዋዕትነትና የተገኘው ውጤት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም::

ተደጋግሞ እንደተነገረውና ሠርቶ አደሩም ሕዝብ እንደሚያውቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ዓላማ የሰው በሰው ብዝበዛና ጭቆናን ማስወገድና አንዱ በሌላው ላብ የሚተዳደርበት የአሠራር ሁኔታ ተደምስሶ ማንኛውም ዜጋ የደከመና የላቡ ውጤት ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሥርዓት ማስፈን ነው::

በፓርቲያችን ፕሮግራም እየታገዝን በየፈርጁ የተያያዝነው ትግል የሚሠምረውና ውጤታማ የሚሆነው ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የአብዮቱን ዓላማ በውል ተገንዝቦ በየተሠማራበት የሥራ መስክ ምርታማ እንዲሆን የበለፀገ ኅብረተሰብ ለመገንባት የጀመርነውን ጥረት ሲያሳካ ብቻ ነው::

ዓላማችን አሮጌውን የፊውዳል ቡርዧ ሥርዓት ከመሠረቱ በመናድና በመገርሰስ አዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት ማስፈን ነው:: አዲሱ ሥርዓትም የዜጎች የወል መብት የሚረጋገጥበትና እኩልነትና የጋራ ብልጽግና የሚሰፍንበት ነው::

...//2

ሊገረሰስ ችሏል ። በዚህ መሠረት በ፲፱፻፷፮ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አብ
ና በር ሊከፍት በቅቷል ።

ወቅት የተደራጀ ግንባር ቀደም አመራር ሰጪ አካል ስላልነበረ ፡ የሠርቶ
ለዩ ለባሹ ክፍል የተውጣጣው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ትግ
ረ ። ከዚያም የዘውድ አገዛዝን በማስወገድና በተከታታይ ልዩ ልዩ አብዮ
አዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት መሠረት ጣለ ። የገጠር መሬት ፣ የከተማ ቦታና

ለኢሕዲሪ ረቂቅ ሕገመንግሥት ውይይት

የሠርቶ አደሩን ተሣትፎ ወሳኝ ነው

የመንግሥት አካላትን አርሶ ጠርሶ የሚያገናኝ
ከዜጎቻቸው ጋራ በህብረት የሚያቆራኝ
ከፍተኛው ህጋዊ ኃይል የህጎች ሁሉ መመንጫ
ህገ መንግሥት ወሣኝ ነው ለበላይነት መገለጫ
የሶሻሊሥት ሕገ መንግሥት አበይት መርህና ይዘት
በመንግሥት ጉዳይ ሕዝቡ ንቁ ተሣትፎ ማሣየት
በተግባር መተርጎሙ ሶሻሊስት ህጋዊነት
በወዛደራዊ መርህ አለማቀፋዊነት
የኮሚኒሥት ፓርቲው ሚና ሲገለፅ ነው በመሪነት
ሐገራችን ካለችበት የኢኮኖሚ ደረጃ
ከጥንታዊ ታሪኳ ከተገኘው መረጃ
ከመደብ ትግሉ አንፃር ከመደቦች የኃይል ሚዛን
ካሉን ብሔረሰቦች ቅንበር በማመዛዘን
ወጥቷል ረቂቅ ሕገ መንግሥቱ እንድንወያይበት
ንቁ ተሣትፎህን አሣይ በመብትህ ተጠቅምበት
ዲሞክራሲያዊ መብትህ በተግባር እንዲረጋገጥ
በኢሕዲሪ ህገ መንግሥት አስተያየትህን እንድትሰጥ
ረቂቁ ቀርቦልሀል የበኩልህን እንድትገልጥ
ሙሉ የሥልጣን ባለቤት የምትሆንበትን
ሙሉ የሥልጣን ባለቤት የምትሆንበትን
የራስህን እድል እራስህን የምትወሰንበትን
የብሔረሰቦች እኩልነት የሚረጋገጥበትን
መብትና ግዴታዎችህ የሚከበሩበትን
አዲሱ በተያያዘው በፖለቲካ ሥርዓት
ለመራመድ እንድትችል በሩ ተከፍቶአል
ለዕለይ መዋቅሩን ለመዘርጋት ለውይይት ቀርቦልሀል
በመሆኑ ተወያይ አስተያየትህን ስጥበት
ተሣትፎህ ወሣኝ ነውና በመብትህ ተጠቀምበት

ጓዱ መንግሥቱ ኃ/ማርያም የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ ዋና ፀሀፊ ፣ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበርና የአብዮታዊ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ፤

በሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሸንጉባኤ መክፈቻ ላይ ሲናገሩ ''ንጉሣዊውን የፊውዳል አገዛዝ ስናስወግድ ምኞታችን በገጽታው ብቻ የተለወጠ ሌላ የፊውዳል አገዛዝ ለማምጣት አልነበረም:: አንዳንዶቹ እንደተመኙት በሕዝብና በዴሞክራሲ ስም የበዘበዛ መሰዕከተችን በማቢደን የካፒታሊስት አገዛዝን ለመትከልም አልነበረም'' በማለት ገልጸው ነበር::

ስለሆነም አብዮቱ ገና ከማለዳው ኢላማ ያደረገው ለሰዎች እኩልነት፣ ለፍትህና ለጋራ ብልጽግና የቆመ መንግሥት ለመመሥረት ነበር::

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የተቋቋመበትዓላማም ይህንኑ ሕዝባዊና ታሪካዊ ግብ እውን ከማድረግ ውጭ እንዳልነበረ እውቅ ነው::


ስለሆነም በዚሁ ጠቀና ትልም መሠረት ከብዙ ችግርና ፈተና በኋላ እነሆ በእውን ሕዝቡን በእርግጥ ጥረው ግረው በወዛቸው የሚተዳደሩ ብዙኃን ዜጎችን በተሟላ ሁኔታ የሚወክል በእነሡና ለእነርሱ የቆመ መንግሥት መመሥረት የምንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል::

በቅደመ አብዮት ኢትዮጵያ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ከመንቃትና ከመደራጀት መሠረታዊ መብት ተገቶ ለመገዛት እንጂ እራሱን ለማስተዳደር ከቶውንም እንደማይችል በተፈጥሮ ሕግ የተበየነበት ተደርጎ ይቆጠር እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው::

ሰፊው ሕዝብ መብቱ በፍጹም ተነፍጎት ስለነበረ የአስተዳደር ዘዴን የተካነ አልነበረም:: በአብዮቱ መባቻ ላይ ልዩ ልዩ ወገኖች በስሙ ተጠቅመው ሥልጣን ለመያዝ የተጣደፉበትም ለዚሁ ነበር::

አሁን በምንገኝበት ሁኔታ ግን ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የተናቀበትና ለተገዥነት ብቻ የተዳረገበት ፣ አስመሳዮች በስሙ ተጠቅመው መልሰው የበዘበዛ ቀንበር ሊጭኑበት የሚችሉበት ሁኔታ የለም::

....//3


...ራቡ ተራማጅ ...ኅብረተሰቡ ክፍሎች በከፈሉት ከፍተኛ ... ሕዝቡ ...ሞቀን
ሊገረሰስ ችሏል ። በዚህ መሠረት በ፲፱፻፷፯ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አብ
...ር ሊከፍት በቅቷል ።

...ት የተደራጀ ማኅባር ቀደም አመራር ሰጪ አካል ስላልነበረ ፡ የሠርቶ
... ለባሹ ክፍል የተውጣጣው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ትግ
...ከዚያም የዘውድ አገዛዝን በማስወገድና በተከታታይ ልዩ ልዩ አብዮ
...ሕዝባዊ ሥርዓት መሠረት ጣለ ። የገጠር መሬት ፣ የከተማ ቦታና

በመጀመሪያ ነገር ሕገ መንግሥት ምንጩ የአንድ ኅብረተሰብ የኢኮኖሚ መሠረት እንደመሆኑ መጠን ይህን መሠረት እያጠናከረ የማሳደግ ሚና ይጫወታል:: ይህም ሥርዓትን በሁሉም መልኩ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊውን ጨምሮ ማረጋገጥ ወይም ማጽናት /ኮንሶሊዴት ማድረግ/ ማለት ነው:: ይህበማንኛውም ዘርዘር ባሉ አነስተኛ ሕጎችም ሁሉ የሚንፀባረቅ ቢሆንም በሕገ መንግሥት ደግሞ ልቆ የሚታይ ሚና ነው::

ሕገ መንግሥት የአዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ ትልቆች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የዕድገት አቅጣጫዎችን ያሳምራል ወይም ይዘረጋል:: ይህ ሚና አብዛኛውን ጊዜ በሶሻሊስትና የሶሻሊስት ዕድገት ፈለግ በሚከተሉ አገሮች ሕገጋተ መንግሥታት የሚንፀባረቅ እንጂ በቡርዣው ሕገ መንግሥት አጦብዛም የሚታይ አይደለም::

ሕገ መንግሥት የማስተማርያ ሠነድ ነው:: የሕገ መንግሥት ይዘትና ሕገ መንግሥት የሚያደኪትታቸው ጉዳዮች ሰፍና በሚገኙው ኅብረተሰብ ርዕዮተዓለም አምሳል የሚቀረጹ ናቸው::

የማሌ ርዕዮተዓለም ተከታይ አገሮች ውስጥ የርዕዮተዓለሙ ዕድገት በኅብረተሰቡ ንቃተ ሕሊና ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠን ሕገመንግሥት በዚህ አኳያ በመቀረጹ የኅብረተሰቡን የንቃ ብቃትና በመጋበዝ መልስ ርዕዮተዓለሙን የማጎልመስና የማስፋፋት ሚና ይጫወታል:: ይህ ሙሉ ለሙሉ በሶሻሊስት ፈርጅ በሚከተተ አገሮች ሕገጋተ መንግሥት የሚታይ ሚና ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት ታሪካዊ መሠረት ፤

በአሥራ ሁለተ የትግል ዓመታት የኅብረተሰቡ ዲሞክራሲያዊ ባህል ዕድገት የፖለቲካ ድርጅት ለማማከል የተደረጉ ትግሎችና የኢሠፓን መከሰት እንዲሁም የኢሠፓን ፕሮግራም በከፍተኛ ደረጃ ያገናዘበ ነው::

ሀገሪቱ ቀደም አብዮትም ሆነ ድኅረ አብዮት በዓለም አቀፍ ግንኙነቶች መስክ ያደረገቻቸውን ውሎችና ስምምነቶም በማመዛዘንና በዓለም አቀፍ የሠራተኛው መደብ ትግልም ውስጥ አገሪተ ሊኖራት የሚገባውን ድርሻ በውል አገናዝቦአል::

የኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት ዓላማ ፤

የረዥሙ አጠቃላይ ዓላማ አገሪቱ በፖለቲካ ፤ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ መስክ የላቀና የተደላደለ ዕድገት ደረጃ ላይ ትደርስ ዘንድ የተጀመረውን ብሔራዊና ዲሞክራሲያዊ አብዮት በማጠናቀቅ ለሶሻሊስት የምርት ግንኙነት መስፈን የጠናከረ መሠረት መጣል ነው።

ይህም በሕገመንግሥቱ ዓላማ ላይ በሚገነባው የሪፐብሊኩ መንግሥት ተግባራዊ ይሆናል። አጠቃላይ ዓላማውም በሽግግር ወቅት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ገንዘቤ ላይ የተመሠረተ የዓለም ሶሻሊስት ሥርዓትን ጉዞ ለማጠናከር የሚያስችል ስልት የሚከተልና በታወቀ ሳይንሳዊ መርሆዎች ላይ የተዋቀረ ነው።

በኢሠፓ ፕሮግራም ላይ እንደተመለከተው የሚዋቀረው ሪፐብሊክ መንግሥት ገላጭ ባህርያት ማለትም ወዛደራዊ ዓለምአቀፋዊነት ፤ ሶሻሊስት ሕጋዊነት፤ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትና የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊና የነቃ ተሳትፎ መርሆዎች በረቂቁ ሕገመንግሥት ,የሚንፀባረቁና የሚረጋገጡ ባህርያት ይሆናሉ።

ለኢሕዲሪ ምሥረታ ወደፊት //

ሰለ ኢህዲሪ ረቂቅ ሕገ. መንግሥት

አ.ጭር. መግለጫ

የ.ጁር ወረዳ የትምህርት የቅስቀሳና

የ.ፕሮፖጋንዳ ኮሚቴ፣ የተዘጋጀ፣

ሰኔ 6 ቀን፣ 1978

ወሳ ቂጤ

ስለኢሕዴሪ ረቂቅ ሕገመንግሥት ሕዝባዊ ውይይት

የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ተሳትፎ ወሳኝ ነው

በቅድመ አብዮት ኢ/ በገጠርና በከተማ ይኖር የነበረው ሰፊው ሕዝብ የመከራና የሰቃይ ኑሮውን እየገፋ ለዘመናት ኖሯል:: ቅድመ አብዮት ኢት/ እጅግ ዝቅተኛና ኃላቀር የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የምትገኝና ማይምነት ረሃብ በሽታ እርዛትና የሠቃይ ኑሮ የሠፈነባት አገር ነበረች::

የአንድ አገር ሰፊ ሕዝብ የግፉ አገዛዝ ሲያስመርረው የፍትህ መዛባት የሰብአዊነት ክብሩን ሲነፍገው የጭቆና ቀንበር ሲያሰቃየው ድህነት ጭካኔና ድንቁርና ሲፈራረቁበት ይህን ከመሰለ ስቃይ ለመውጣት የሚነሳበት ጊዜ ተገንና ምርኩዝ የሚያደርገው አንድነቱንና ኃይሉን ነው::

በመሆኑም የኢትዮጵያም አብዮት ጊዜው ያስፈለገበት የኃ/ሥላሴን መንግሥት ጥሎ በምትኩ ጭቆና የሌለበትን ሥርዓት ለመመሥረት ቆርጦ ሲነሣ ደረጃ በደረጃ ሠፊውን ሕዝብ ለሥልጣን ባለቤትነት የሚያበቁትን በርካታ እርምጃዎች ወስዷል::

ሠፊው ሕዝብ በመረጠው ትክክለኛ የዕድገት ጎዳና መጓዝ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ድሎችን ተቀዳጅቷል:: ከእነዚህም ድሎች በተለይም ሆነ በጥቅሉ ሲታዩ በኢት/ ኅብረተሰብ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ መዋቅርና ፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ መድረሱን በግልጽ የሚያመለክቱ ከመሆናቸውም በላይ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ቁሳዊ ሕይወቱ እየተለወጠ ለተፋጠነ ማኅበራዊ ዕድገት የሚያስችለውን መሠረት የተጣለበት መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው::

አሥር ዓመቱ ፕሮግራም በግልጽ እንዳስቀመጠው "የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማኅበራዊ መሠረት በሠራተኛውና በገበሬው ኅብረት በአብዮታዊ ምሁር በአብዮታዊ ሠራዊት ለአብዮቱ ዓላማ በቆሙ የእጅ ጥበብ ሙያተኞችና በጥቃቅን ሠራተኞች ተባባሪነት የሚገለፅ ይሆናል:: ይህም ሁኔታ ሠርቶ አደሩ የበላይ ገዥነቱን መጎናጸፊያ ቁልፍ ነው::

ይህን ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ለመመሥረት ሕገ መንግሥት ስለሚያስፈልግ በአዋጁ የተቋቋመው የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን 4 ክፍሎች 17 ምዕራፎችና 120 አንቀጾች ረቂቁን አዘጋጅቷል::

ይህም ረቂቅ ሕገ መንግሥት በጸደረቀው ከሀገር አቀፍ ጀምሮ ሲሚናሮች ተደርገውበት በሁኑ ወቅት ለሰፊው ሕዝብ ውይይት ቀርቧል:: ሠፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ በሕዝባዊ ውይይት ወቅት የሕዝቡን ተሳትፎ ረቂቅ ሕገ መንግሥቱን በማዳበሩም በሸገር የሠፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት ማረጋገጫ መድረክ ነው::

ስለ ሕገ መንግሥት ፅንሰ ሀሳብ የቀረበ አጭር ማብራሪያ

ሕገ መንግሥት እንደየሥርዓቱ ማህበራዊ ዓይነትና ኅብረተሰቡ እንደደረሰበት የዕድገት ደረጃ አንዱ መንግሥት የሚመሠረትበትና የአንድን ኅብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች የሚገዙ መርሆዎችን የሚደነግግ መሠረታዊ ሕግ ነው::

— ሕገ መንግሥት በመደባዊ ባሕርይው ሲታይ በሁለት ይከፈላል:: እነርሱም የቡርዧ ሕገ መንግሥትና የሶሻሊስት ሕገ መንግሥት ናቸው::

የቡርዧ ሕገ መንግሥት ለዜጎች መሠረታዊ ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና የነፃነቶችን ለይሰጣል የሚመስል ቢሆንም የካፒታሊዝምን የምርት ግንኙነት የቡርዧውን የግል ሀብት ይዞታና የፖለቲካ የበላይነት ከማስጠበቅ አያልፍም::

ዛሬ ብዙኃኑ ሕዝብ አብዮቱ ባጎናፀፈው መብት እየተጠቀመ በሥልጣን ሙሉ ባለቤትነት እራሱን በራሱ ለማስተዳደር መቻሉን በተግባር የሚያረጋግጥበት ሁኔታ ላይ ደርሶአል:: ስለሆነም ከእንግዲህ የተሟላ ልዕልናውን ለማረጋገጥ የሚቀረው የመጨረሻውን ወሳኝ እርምጃ ማራመድ ብቻ ነው::

ከአብዮቱ መነሻ ወቅት ጀምሮ ከፍተኛ ትግል የተደረገው እውነተኛና ለሠርቶ አደሩ የጋራ ብልጽግናና ዋስትና የሚቆም መንግሥት ለመመሥረት ነው:: ይህም መንግሥት ለፍቶ አዳሪውን ሕዝብ ለዘላቂ ምኞት ለማብቃት በግንባር ቀደምትነት ከሚመራው ፓርቲና እንዲሁም ሕዝቡ ኃይሉን ካስተባበረባቸው ሕዝባዊ ድርጅቶች ጋር በአንድነት በሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ የታቀፈና የመላውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ፍላጎት የሚያስፈጽም ነው::

በአብዮታዊት ኢትዮጵያ በቅርቡ በሕዝባዊ ውይይት ዳብሮና የመጨረሻ ቅርጽና ይዘቱን በማግኘት በውሳኔ ሕዝብ /ሪፈረንደም/ የሚፀድቅ ረቂቅ ሕገመንግሥት መዘጋጀቱ ተደጋግሞ የተገለፀና ከብሔራዊ ደረጃም ጀምሮ በስፋት ውይይት የተደረገበት ነው::


ስለሆነም ስለሕገመንግሥት ምንነትና በታሪክ ሂደት ሕገመንግሥት መቸ እንደ ተከሰተ ማመልከት አስፈላጊ ነው::

ስለ ሕግ መሠረተ ሃሳብ፤

ስለ ሕገ መንግሥት ከማውሳታችን በፊት ሕግ ምን ማለት እንደሆነና ምንጩስ ምን እንደሆነ አጭር ቅኝት ማድረግ ተገቢ ይሆናል::

ሕግ ማለት በኅብረተሰብ እድገት ታሪክ ውስጥ የተወሰነን የመደቦች ግንኙነትና በግንኙነትም ሳቢያ የሚፈጠሩ ክስተቶችን የሚገዛ ወይም የግንኙነታቸውን ስፋትና ጥልቀት የሚወስን ዘላቂም ባይሆን ክስተቶቹ እስካሉ ድረስ አንፃራዊ የዕድሜ ቆይታ ያለው የምግባር ደንቦች ጥንቅር ነው::

የመደቦችና የሕግ ግንኙነት፤ በአጠቃላይ አነጋገር በታሪክ ውስጥ ከመደቦች አመጣጥ ጋር አብሮ የተወሰደ እንደየኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ በወቅቱ ሰፍኖ ከሚታየው


ተራማጅ ፣ ኅብረተሰቡ ክፍሎች በከፈሉት ከፍተኛ ሕዝቡ ... ሊገረሰስ ችሏል ። በዚህ መሠረት በ፲፱፻፷፮ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አብ
... በር ሊከፍት በቅቷል ።

... ቅት የተደራጀ ግንባር ቀደም አመራር ሰጪ አካል ስላልነበረ ፣ የሠርቶ
... ለባሹ ክፍል የተውጣጣው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ትግ
... ከዚያም የዘውድ አገዛዝን በማስወገድና በተከታታይ ልዩ ልዩ አብዮ
... ሕዝባዊ ሥርዓት መሠረት ጣለ ። የገጠር መሬት ፣ የከተማ ቦታና

የኢኮኖሚ ግንኙነት የሚመነጭና በወቅቱ የበላይነት ያለውን መደብ ፖለቲካዊ ሥልጣንና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስከብር ነው፡፡

በመሆኑም የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ግንኙነቶችን በመወሰን ረገድ በፊውዳሉ ኅብረተሰብ ሥልጣን በዘውድ አገዛዝ ሥር እንደሚወድቅና ይህም ሥልጣን በወራሴ መንግሥት በትውሉድና በዘር ሐረግ እንደሚተላለፍ፣

በመሬት የኢኮኖሚ መሠረት ላይ የተገነባውን የምርት ግንኙነት ዘላቂነት ለመጠበቅ የመሬት ከበርቴውን የጭሰኛውን ግንኙነት በመደንገግ በሥርዓቱ ኢኮኖሚው ውስጥ ያላቸውን ሚና የሚያመለክት ይሆናል፡፡

<u>የቡርዧው ኅብረተሰብ ሕግ ፣</u> በቡርዧ ኅብረተሰብ ውስጥ ሥልጣን በምርጫ የሚጨበጥ ቢሆንም ምርጫው ለተወሰኑ የግል ንብረት ባለቤትነት ላላቸው ክፍሎች ብቻ የተከፈተና የቡርዧውን መደብ የበላይነት ለማስከበር በሚቀርፁ የውክልና መድረኮች በፖርላማ ተግባር እንደሚውልና የግል ንብረትን መሠረቱ አድርጎ በሚቀረው የምርት ግንኙነት ውስጥ ዓቢይ መደቦች ሆነው የሚከሰቱት የወዝ አደሩን ወይም የሠራተኛውንና የቡርዧውን መደብ ግንኙነት የሚገዛና በኢኮኖሚ ሥርዓቱም ውስጥ ያላቸውን ሥፍራ የሚደነግግ ይሆናል፡፡

<u>የሶሺሊስት ሕግ ፣</u> በሶሻሊስት ኅብረተሰብም ውስጥ የሰፊው ሕዝብ መንግሥት በኅብረተሰቡ መሳ ተሳትፎ እንደሚቀርና በዚህ የመንግሥት አስተዳደር ውስጥም ሕዝቡ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን ሥልጣን እንደሚኖረው ፣

በዚህም ሥልጣኑ የመላው ሠርቶ አደርና ማኅበራዊ ይዘት ያለውን የምርት መገልገያ ባለቤትነት የማስፋት በሁሉም መልኩ ብዝበዛ አልባ ኅብረተሰብ ለመገንባትና የሠራተኛውን መደብ የበላይነት እንደሚያረጋግጥ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም እንደየኅብረተሰቡ ደረጃ የተለያዩ ቅርጽ ይኑረው እንጂ በጥቅሉ ሕግ የኅብረተሰቡን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ግንኙነት የሚወስን ፣ የበላይነት ያላቸውን መደቦች ጥቅም የሚያስከብር የንብረት ግንኙነት ሳቢያ የሚፈጠሩ ነባራዊ ግንኙነቶችን ሕጋዊ ቅርጽ የሚሰጥ የመንግሥት መሣሪያ ነው፡፡

...//5

...ተራማጅ ... ክፍሎች በከፈሉት ከፍተኛ
...ሊገረሰስ ችሏል ። በዚህ መሠረት በ፲፱፻፷፯ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አብ...
...ር ሊከፍት በቅቷል ።

...ት የተደራጀ ግንባር ቀደም አመራር ሰጪ አካል ስላልነበረ ፡ የሠርቶ...
...ለባሹ ክፍል የተውጣጣው ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ትግ...
...ዜያም የዘውድ አገዛዝን በማስወገድና በተከታታይ ልዩ ልዩ አብዮ...
... ሕዝባዊ ሥርዓት መሠረት ጣለ ። የገጠር መሬት ፣ የከተማ ቦታና